<u>ርዕሰ አንቀጽ</u>

# አሥራአንደኛው ዓመት - 2011፣

በ21ኛው ክፍለ ዘመን 11ኛው ዓመት፣ 2011 በሰው ልጆች ማህበራዊ ግንኙነትና ሥርዓተ-አስተዳደር ለውጥ ሂደት ላይ አዲስ ጅምር ፈጥሮ አለፈ። ምንም እንኳን በየዘመናቱ በተከናወኑት የለውጥ ሂደቶች በአሮጌነት የታለፉ ልዩ ልዩ የምርት ግንኙነቶችና ሥርዓተ-ደምቦች በተለያዩ ሀገሮች ውስጥ እስካሁንም ጨርሰው ሳያከትሙ በአዝጋሚነትና በጥገኝነት ሲንፀባረቁ ቢታዩም፣ ከ18ኛው ክፍለ ዘመን በፊት ሰፍኖ የነበረው የመሬት ከበርቴ ሥርዓትና የምርት ግንኙነት በዚሁ ዘመን መደምደሚያና በ19ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ የአዲስ ሥርዓትን ለውጥ በሻተ የእርስ በርስ ጦርነትና አብዮት አመካይነት ታዳጊ ሆኖ በመጣው የካፒታላዊ ሥርዓት ተተካ። እንደዚሁም ደግሞ በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ በተቀነቀነው የማህበረሰባዊነት አብዮት አዲስ ሽግግር ተደርጎ ዓለማችንን ለረዥም ጊዜ ከፍሎት የቆየውን የምስራቅ-ምዕራብ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ሚዛን ፈጥሮ ቆይቷል።

አሁን በጀመርነው 21ኛው ክፍለ ዘመን ደግሞ መቋጫው ምን ሊሆን እንደሚችል በእርግጠኝነት መናገር ባይቻልም፣ ለአዲስ ሥርዓተ-ህግና የምርት ግንኙነት አዲስ ክስተት መታየት ጀምሯል። የዘመናችን አዲስ ክስተት ጅምር የአዲስ ሥርዓተ-ህግና የምርት ግንኙነት ጥያቄ ቀዜማ መሆኑን የሚያበሥረው፣ ሽግግር ከተደረገባቸው ካለፉት ዘመናት ጥያቄዎችና ሕዝባዊ እንቅስቃሴዎች ጋር ተመሳስሎ ስለሚገኝ ነው።

በመሬት ከበርቴው ሥርዓት ዘመን አመዛኙ የምርት ግንኙነት የሚገለጸው ጉልበቱንና ጊዜውን በ"ፊቃደኝነት" በሚሸጠው ገባርና የመሬትና የማምረቻ መሳሪያዎች ባለቤት ከሆነው ሃብታም ጋር በሚደረግ ትሥሥር ነበር። ለልማት የዋለው የመሬት ክፍል፣ የማምረቻ መሳሪያዎች ባለቤት በሆኑ ጥቂቶች እጅ እየሆነና የህብረተሰብ ቁጥር እየናረ ሲመጣ፣ ነገሥታቱና መኳንንቱ የተቀማጠለ ኑሯቸውን ለመምራት ያስችላቸው ዘንድ በሚጥሉት ከፍተኛ ግብርና ታክስ ምክንያት የአብዛኛው ኑሮ ከእጅ ወደ አፍ እየሆነ ሲመጣ፣ የምርቱ ክፍፍልና ስርጭት የሥርዓቱን ሚዛንና ህልውና ሊያስጠብቅ አልቻለም። በሮጌው ሥርዓት ውስጥም የሚያቀጠቁጡት ታዳጊ የማምረቻ ስልቶች፣ ማህበራዊ እይታዎችና አስተሳሰቦች አስሮ ከያዛቸው ሥርዓት ፈልቅቀው ለመውጣት ከሚያደርጉት ከፍተኛ ጥረት ጋር የሰፊው ሕዝብ ጭቆናና ብዝበዛ ተዳምሮ በተካሄደ ትግል የነበረው የምርት ግንኙነትና ሥርዓተ-ህግ ከማይቀጥልበት ደረጃ ደርሶ ታዳጊ ለሆነውና የህብረተሰቡን ምርታማነትና ፍጆታ ወደሚያቻችል አዲስ ሥርዓት አመራ። የካፒታሊስቱ ሥርዓት ጅምር ብዙ ሕዝብ ወደ ተግባራዊ ሥራ ማሠማራትና በአንድ ጊዜ የተለያየ ነገር በብዛት ማምረትና ማከፋፈል በመቻሉ ካረጀው ጉልታዊ ሥርዓትና የመሬት ባለቤት/ገባር ግንኙነት መሻሉን አሳየ። እየቆየም ሳይንስና ተክኖሎጂ እየዳበረ ሲመጣ ህብረተሰብ በእምርታዊነት ወደ አዲስ ዘመን ተሸጋገረ፤ የካፒታሊዝም ስልተ-ምርት ሁሉም ሊደርስበት የሚሻው ገዥ ሥርዓት ሆነ። ይሁን እንጅ እያደገና ሥር እየሰደደ በመጣው የካፒታሊዝም ሥርዓት ውስጥ አሁንም ጥቂቶች እየተመነደጉ፣ ብዙዎች እየጫጩ የመጡበት፣ የሰው ልጆች መብትና ነጻነት በገንዘብና በሃብት እየተመነዘረ የመጣበት፣ ህጻናትና ሴቶች ለብዝበዛና ለአደጋ የተጋለጡበት፣ ወዘተ... እየሆነ መጣ። ይኸም የ20ኛውን ክፍለ ዘመን ህብረተሰባዊነት እንቅስቃሴና አብዮት አበረታታ። የህብረተሰባዊነት አብዮቱ ውጤት ምንም እንኳ ወደ ሁዋላ ብዙዎች የጠበቁትን እኩልነትና መብት ሙሉ በሙሉ ባያጎናጽፍም ብዙ ሀገሮችን ከቅኝ ተገዥነት እንዳላቀቀና በሳይንስና ወታደራዊ አቅም ግንባታም ቀደም ሲል ሶቬት ህብረትን እስካሁንም ቻይናን በአጭር ጊዜ ውስጥ

እንዳመጠቀ ተስተውሏል። ይህ ጅምር በመውደቅ በመነሳት ላይ ያለ ክስተት መሆኑ ዛሬ የሚታይ ሲሆን፣ ለረጅም ጊዜ ገኖ የቆየውና በብዙ ዘርፎች ከፍተኛ ግስጋሴ ያደረገው የካፒታሊስት ሥርዓት ግን በአሁኑ ሰዓት ከሁሉም አቅጣጫ ተሰቅዞ በመያዝ እንዳለፈው የእርምጃ መጠኑ በተመሳሳይ ሁኔታ ወደፊት መንቀሳቀስ አለመቻሉ እውን እየሆነ ነው። ዋናው የችግሩ ሽምቀቆ በሰፊው ሕዝብና ካፒታሉን የተቆጣጠሩት ትቂት የናጠጡ ግለሰቦችና ድርጅቶች በፈጠሩት ችግርና በመካከላቸው ያለው "የሰማይና የምድር ያህል" የተራራቀ የገቢ መጠን መሆኑ ግልጽ ሆኖ ወጧል። ሃብትን በመፍጠርና በማሳደግ የተዋጣለት የካፒታሊስት ሥርዓት ከፍተኛ የቴክኖሎጅ እድገት ላይ በመድረሱና በዚህም በመታገዝ ከጉልበት ይልቅ ቴክኖሎጅውን እየተጠቀመ ሠራተኛውን ሃይል ተንሳፋፊና ሥራፈት አደረገው። ከእጅ ወደ አፍ የሚኖረው አብዛኛው ሕዝብ ካፒታሉ ያለበቃኝና ደከመኝ የሚያመርተውን የአገልግሎትና የሸቀጥ ምርት የመግዛት አቅም ማነስ ብቻ ሳይሆን በአራጣና በወለድ ለያዛቸው መገልገያዎቹና መኖሪያ ቤቶቹ እንደገባው ውል መጠን ለመክፈል አቅም አነሰው፤ በውል(በስምምነት)ማፍረስ ምክንያት ሕዝቡ በአበዳሪዎቹ ይዞታውን ተነጥቆ መገልገያና መጠለያ ቤቱን እያጣ ሜዳ ላይ ፈሰሰ። አሜሪካን መሠረት አድርጎ በአደጉት አገሮች ውስጥ የተፈጠረው የኢኮኖሚ ቀውስ፣ በካፒታሉ ተጽእኖ ሥር በነበረው የቀረው ዓለም ኢኮኖሚ ላይም ተመጣጣኝ ችግር ፈጠረ። ለአደጉት አገሮች ካፒታል ጥገኛ ሆነው በየሀገሮቻቸው ያዙ ይናዙ የነበሩ አምባገነኖች ከሚፈጽሙት የሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ጥሰት በተጨማሪ ሕዝባቸው በኢኮኖሚ ድቀት አደጋ ውስጥ እንዲገባ አመቻቹት። በብድርና በልመና ይግኝ የነበረ ገቢ እየተመናመነ በመምጣቱ ለሰፊው ሠራዊታቸውና ቢሮክራሲያቸው የሚከፍሉት ገንዘብ እያጠጠ መጣ። ሃላፊነት በጎደለው ሁኔታ የሚያገሽፉት ሀገራዊ ገንዘባቸውም የገበያ ላይ እቃዎችን እጅግ እንዲወደዱ አደረጋቸው፤ በዚህም ሰፊው ድሃ ሕዝብ የመግዛት አቅም አጣ፤ ኑሮ ምስቅልቅል ብሎበት መውጫ ፈለገ።

ከላይ የተጠቀሱት ሁኔታዎች ቀስ በቀስ እያደጉ መጠው በ2011 ዓ.ም ላይ በዓለም አቀፍ ደረጃ በተለያዩ ሀገሮች ውስጥ የሕዝብ ቁጣ ገነፈለ። በዚሁ ዘመን በ11ኛው ዓመት መጀመሪያ ላይ በሰሜን አፍሪካ የተቀጣጠለው ሕዝባዊ አመጽ የቱኒሲያውን አምባገነናዊ ሥርዓት የዚን እል አቢዲን ቢን አሊን (Zine El Abidine Ben Ali) መንግሥት "ሀ" ብሎ አሰወገደ። ሕዝባዊ አመጹ ትዕይንቱን አስፍቶ በመቀጠልም እስከ ዓመቱ መጨረሻ የግብጹን አምባገነን የሆስኒ ሙባራክን (Hosni Mubarak) የጭቆናና የአፈና ሥርዓት በአጭር ቀናት ውስጥ ለውጦ ብዙ ደም ባፋሰሰ ሁኔታም የሊቢያውን የኮሎኔል ሟማር ጋዳፊና (Muammar Gaddafi) እና የየመኑን የአሊ አብዱላህ ሳለህን (Ali Abdullah Saleh) መንግሥቶች ከሥልጣን አስወግዷል። ሕዝባዊ መንሳሳቶችና ጠንካራ ተቃውኖዎች በሶሪያ፣ ባህሪይን፣ አልጀሪያ፣ ኢራቅ፣ ጆርዳን፣ ኩዌት፣ ሞሮኮ፣ አማን፣ ሊባነን፣ ሞሪታኒያ፣ ሳውዲ አረቢያና ሱዳንን አካቶ ሰላማዊ ሰልፎችና ሕዝባዊ እንቅስቃሴዎች የታዩ ሲሆን ለሌሎች አምባገነንና ጨካኝ የአፍሪካ መሪዎችም ለአይቀሬነቱ "ቢጫ ካርድ" አሳይቷል።

በአውሮፓና ሰሜን አሜሪካም በተዛባው የኢኮኖሚ ፖሊሲ የተጎዳውና ሥርዓቱ የፈጠረው የገቢ መራራቅ ያሳሰበው የህብረተሰብ ክፍል አደባባይ በመውጣት ጠንካራ ተቃውሞና ሰፊ እንቅስቃሴ አሳይቷል። ቀጣዩ ዓመት ምን ሊመስልና ሊሆን እንደሚችል በሂደት የሚታይ ቢሆንም፣ አሁን በዓለማችን ላይ ሰፍኖ ያለው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሥርዓት ግን የግድ በተሻለ ሁኔታ መተካትን የሚጠይቅ መሆኑን የዘመናችን 11ኛው ዓመት፣ 2011 አስገንዝቦ አልፏል። ኢትዮጵያችን ጨምሮ በአምባገነን መንግሥታት ቀንበር ሥር ያሉ ሕዝቦች ጊዜውን በወቅቱ ከተጠቀሙበት ከፊታቸው ብሩህ ጊዜ የተደቀነ መሆኑንም ይህ ያለፍነው የዘመናችን 11ኛ ዓመት ምልክት አሳይቷል። በሕዝብ ስም ለሕዝብ የተሟላ መብት እንታገላለን የሚሉ ወገኖችም አያልፉት ዕድል አጋጥሟቸዋልና ሃላፊነታቸን ለመወጣት ይምከሩ፣ ይሰቡበት እንላለን።